የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
አዲስ አበባ ሐምሌ ፭ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No.39
ADDIS ABABA 12th July, 2022

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፲፯/፪ሺ፲፬

የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………………………ገጽ ፲፬ሺ፪፻፷፱

ደንብ ቁጥር ፭፻፲፯/፪ሺ፲፬

## ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹/፪ሺ፲፪ አንቀጽ ፲፯ እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፱/፪ሺ፯ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፩፻፳፱(፮) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፲፯/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## Content

Regulation No. 517/2022

Council of Ministers Investment Incentive Regulation …….............................Page 14269

## REGULATION NO. 517/2022

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR INVESTMENT INCENTIVES

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 17 of the Investment Proclamation No. 1180/2020 and Article 129(6) of the Customs Proclamation No. 859/ 2014 (as amended).

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as "Council of Ministers Investment Incentive Regulation No. 517/2022".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 309:00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፪. ትርጓሜ**

በአዋጁ ለቃላት እና ሀረጎች የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ **"የታክስ ማበረታቻ"** ማለት በዚህ ደንብ መሠረት ለማበረታቻ ብቁ ለሆነ ኢንቨስትመንት የሚሰጥ ከገቢ ግብር ወይም ቀረጥ ነፃ የመሆን መብት ነው፤

፪/ **"ነባር ኢንቨስትመንት"** ማለት የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም ሌላ አግባብነት ያለው ፈቃድ ኖሮት በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለ ድርጅት ነው፤

፫/ **"አዋጅ"** ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹/፪ሺ፲፪ ነው፤

፬/ **"የካፒታል ዕቃ"** ማለት ለሽያጭ የሚውሉ ምርቶችን ለማምረት ወይም አገልግሎቶችን ለመስጠት ጥቅም ላይ የሚውል መሣሪያን እና እነዚህን የመሳሰሉ ግዙፋዊ ሀልዎት ያላቸውን ሌሎች ንብረቶች ይጨምራል፤

፭/ **"የግንባታ ዕቃ"** ማለት የህንጻ ወይም የግንባታ ሥራ አካል የሚሆን ለግንባታ ሥራ የሚውል ዕቃ ወይም አቅርቦት ነው፤

፮/ **"ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤት"** ማለት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የማዕድን ሚኒስቴር፣ የክልል፣ የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤቶች፣ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ የገቢዎች ሚኒስቴር እና ሌሎች የኢንቨስትመንት ማበረታቻ አፈፃፀምን ለመቆጣጠር በሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ናቸው፤

**2. Definition**

Without prejudice to the words and phrases defined under the Proclamation, for the purposes of this Regulation:

1/ **"Tax Incentive"** means any tax or duty incentives right granted to eligible investment under this Regulation;

2/ **"Existing Investment"** means an investment on which an investor has acquired business license or any other license and is engaged in production or service rendering activities;

3/ **"Proclamation"** means the Investment Proclamation No. 1180/2020;

4/ **"Capital Good"** includes equipment and other similar tangible goods used to produce goods or render services for consideration;

5/ **"Construction Material"** means a material or supply that is to be made part of a building or any other construction;

6/ **"Regulatory Institution"** means the Ethiopian Investment Commission, Ministry of Mines, Regional Governments and Addis Ababa and Dire Dawa City administrations Investment Organs, Ministry of Trade and Regional Integration, Ministry of Revenue and other Institutions mandated to regulate the implementation of tax incentives;

፯/ **"የገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የክልል መንግሥታት እንዲሁም የድሬዳዋ እና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድሮች የታክስ ባለሥልጣናት ናቸው፤

፰/ **"የገቢ ግብር"** ማለት በፌደራል ወይም በክልል መንግሥታት የገቢ ግብር አዋጆች በሠንጠረዥ "ሐ" በተመለከተው ገቢ ላይ የተጣለ ግብር ነው፤

፱/ **"ቀረጥ"** በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፱/፪ሺ፮ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፤

፲/ **"ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

## ፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

፩/ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች የታክስ ማበረታቻ በሚያስገኙ መስኮች ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት በሚሰጡ የገቢ ግብርና የቀረጥ ማበረታቻዎች ብቻ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

፪/ በዚህ ደንብ ክፍል አራት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች በማዕድን፣ በነዳጅ እና በጂኦተርማል ኢንቨስትመንት ላይም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ</u>

### ፬. <u>ለአዲስ ኢንቨስትመንት ስለሚሰጥ ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ</u>

፩/ አዲስ ኢንቨስትመንት ለማቋቋም ኢንቨስት የሚያደርግ ባለሀብት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡



7/ **"Tax Authority"** means the Ministry of Revenue or the tax authorities of the Regional Governments as well as the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

8/ **"Income Tax"** means the income tax imposed on schedule "C" under the Income tax laws of the Federal or Regional governments;

9/ **"Duty"** shall have the meaning provided to it under Customs Proclamation No. 859/2014;

10/ **"Ministry** or **Minister"** means the Ministry or the Minister of Finance respectively.

## 3. <u>Scope of Application</u>

1/ The provisions of this Regulation shall apply to Income Tax and Duty incentives granted to encourage investment in sectors eligible for incentives;

2/ Without prejudice to the provisions of Part Four of this Regulation, other provisions of this Regulation shall also apply on investments in mining, petroleum and geothermal sectors.

## <u>PART TWO</u>

## <u>INCOME TAX EXEMPTION INCENTIVE</u>

### 4. <u>Income Tax Exemption for New Investment</u>

1/ Any investor who invests to establish a new business shall be entitled to income tax exemption as provided for in the schedule attached hereto.

፪/ የገንዘብ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር በሚያወጣው መመሪያ ዝርዝራቸው በሚወሰን ከመሐል ኢትዮጵያ ርቀው በሚገኙ እና/ወይም ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ችግር ባለባቸው አካባቢዎች፤

ሀ) አዲስ ኢንቨስትመንት ለማቋቋም ኢንቨስት የሚያደርግ ባለሀብት በሠንጠረዡ በተመለከተው መሠረት የሚያገኘው የገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ለሦስት ተከታታይ ዓመታት በየዓመቱ የ፴ በመቶ የገቢ ግብር ቅናሽ ይደረግለታል፤

ለ) በአዳዲስ፣ ባልተለመዱ እና በተመረጡ የቱሪዝም መዳረሻዎች ቦታዎች የኮከብ ደረጃ ባላቸው የሆቴል፣ የሎጅ እና ሪዞርት አገልግሎት መስጫ ዘርፎች ኢንቨስት ለሚያደርግ ባለሀብት የ፭ (አምስት) ዓመት የገቢ ግብር እፎይታ ይሰጣል፡፡

፫/ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በማዕድን እና ነዳጅ መስክ የሚደረግ ኢንቨስትመንት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ አያስገኝም፤

፬/ በውጭ ሀገር በሥራ ላይ የሚሰማሩ ሰዎችን ለማሰልጠን ሕጋዊ እውቅና ካላቸው የሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞችን ወደ ውጭ ሀገር በመላክ፡-

2/ An investor who invests in areas far from the center and/or with very low infrastructure development that are listed in a Directive to be issued by the Ministry of Finance in consultation with concerned stakeholders shall:

a) be entitled to an income tax deduction of 30% for three consecutive years after the expiry of the income tax exemption period specified in the schedule attached hereto;

b) be entitled for a five year income tax exemption if invests in new, atypical and selected tourist destination areas in hotels, lodges and resorts with a rank of a star.

3/ Without prejudice to the Schedule attached to this Regulation Income Tax exemption shall not be granted to mining and petroleum activities;

4/ An investor who provides employment opportunities outside of Ethiopia to Ethiopians who have obtained qualification certificate from an institution recognized for providing training to persons who are to be placed in a foreign country shall:

ሀ) ከ፩፻-፫፻ ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል ያስገኘ ባለሀብት ለአንድ ዓመት፤

ለ) ከ፫፻፩-፭፻ ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል ያስገኘ ባለሀብት ለሁለት ዓመት፤

ሐ) ከ፭፻፩ በላይ ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል ያስገኘ ባለሀብት ለሶስት ዓመት፤

ከንግድ ትርፍ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናል፤

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፬) የተደነገገው ተፈፃሚ የሚሆነው ባለሀብቱ ሠራተኞቹ ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ያደረገ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ከሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር እንዲሁም የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሲያቀርብ ይሆናል፤

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፬) መሠረት አንድ ባለሀብት የሚያገኘው ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ በድምሩ ከስድስት ዓመት የበለጠ ሊሆን አይችልም፤

፯/ የገንዘብ ሚኒስቴር በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያምንበት ማበረታቻ በሚያስፈልገው የኢንቨስትመንት መስክ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ተገቢውን ማበረታቻ እንዲያገኙ በመመሪያ ሊፈቅድ ይችላል፡፡



a) be entitled for one year income tax exemption if provides employment opportunity for 100-300 Ethiopians;

b) be entitled for two years income tax exemption if provides employment opportunity for 301-500 Ethiopians;

c) be entitled for three years income tax exemption if provides employment opportunity for over 501 Ethiopians;

5/ The provisions of Sub-Article (4) of this Article shall apply when the investor submits evidence from the Ministry of Labor and Skill showing that it has secured employment opportunities to such employees for not less than one year as well as renewed business license;

6/ The income tax exemption to be granted to an investor under Sub-Article (4) of this Article shall not exceed six years;

7/ The Ministry of Finance may for good cause grant income tax exemption by Directive to investors who invest in investment sectors that need to be incentivized.

## ፭. ለነባር ድርጅት ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ ስለሚሰጥ የገቢ ግብር ማበረታቻ

፩/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት ማበረታቻ በሚያስገኝ መስክ ነባር ኢንቨስትመንቱን ያስፋፋ ወይም ያሻሻለ ባለሀብት ከማስፋፊያው ወይም ከማሻሻያው የሚያገኘው ተጨማሪ ገቢ ከዚህ ደንብ ጋር የተያያዘውን ሠንጠረዥ መሠረት በማድረግ የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት ያገኛል፤

፪/ ነባር ድርጅትን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የሚሰጠው ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ ተጠቃሚ መሆን የሚቻለው አግባብነት ባለው ተቆጣጣሪ አካል፡-

ሀ) ነባሩ ድርጅት በኢንቨስትመንት ፈቃዱ መሠረት ለማምረት ያቀዳቸውን የምርት ዓይነቶች ወይም የምርት መጠን እና ሌሎች ቅድመ-ሁኔታዎችን ማሟላቱ፤

ለ) ማስፋፊያው እና ማሻሻያው ሚኒስትሩ በዚህ ደንብ መሠረት በሚያወጣው መመሪያ የተቀመጡ የመመዘኛ መስፈርቶችን ማሟላቱ፤

ሐ) የነባር ድርጅቱን የኦዲት ሪፖርት በማቅረብ ኢንቨስተሩ ግዴታውን በአግባቡ የተወጣ መሆኑ፤

ሲረጋገጥ እና ከማሻሻያው ወይም ከማስፋፊያው ለተገኘው ተጨማሪ ገቢ ብቻ ሲሆን፤ ይህም ገቢ ተለይቶ በሒሳብ መዝገብ መታየት አለበት፡፡

## 5. Income Tax Exemption for Expansion or Upgrading of Existing Investment

1/ Any investor expanding or upgrading his existing investment pursuant to Sub-Article (2) of this Article shall, with respect to the additional income generated by the expansion or upgrading, be entitled to income tax exemption as provided in a Directive to be issued by the Ministry of Finance on the basis of the schedule attached hereto;

2/ An investor expanding existing investment shall be entitled to income tax exemption for the expansion or upgrading of existing investment upon ascertaining by the relevant Regulatory Institution that:

a) the existing investment has achieved the type and volume of product and other preconditions as per the investment license;

b) the expansion or upgrading fulfills the eligibility criteria provided in the Directive issued by the Ministry;

c) the investor has submitted audit reports that shows the proper fulfillment of the obligation of the existing investment;

and such incentive shall be allowed only for the income from the expansion and upgrading which shall be shown in a separate books of account.

**፮. ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት ስለሚሰጥ ተጨማሪ የገቢ ግብር ማበረታቻ**

፩/ ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጪ ያለ ኢንቨስትመንት ሆኖ ቢያንስ ፷ በመቶ የሚሆነውን ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ወደ ውጭ የሚልክ ወይም ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት በምርት ወይም በአገልግሎት ግብዓትነት የሚያቀርብ ከሆነ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ከተፈቀደለት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ በተጨማሪ ለአንድ ጊዜ ለሁለት ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ ይሆናል፤

፪/ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ኢንቨስት ያደረገ ባለሀብት ካቋቋመው የማምረቻ ፋብሪካ ፹ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆነውን ምርት ወደ ውጭ ሲልክ ወይም ምርቱን ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት በምርት ግብዓትነት የሚያቀርብ ከሆነ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ከተፈቀደለት በተጨማሪ ለአንድ ጊዜ ለሁለት ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ ያገኛል፡፡

**፯. የገቢ ግብር ማበረታቻን በሌላ ስለመተካት**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዚህ ደንብ የተቋቋመውን የገቢ ግብር የማበረታቻ ዓይነት በሌላ የማበረታቻ ዓይነት ሊተካው ይችላል፡፡

**፰. በገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ ዘመን ገቢን ስለማሳወቅ**

፩/ ማንኛውም ባለሀብት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬፣ ፭፣ እና ፮ ለተመለከቱት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻዎች ተጠቃሚ የሚሆነው በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሒሳብ መዝገቡን አግባብ ላለው የግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ሲያቀርብ ይሆናል፤

**6. Additional income Tax Exemption for Investors Exporting Products or Services**

1/ Any investor who has invested outside of the industrial parks and who exports or supplies to an exporter as production or service input, at least 60% of his products or services shall be entitled to a one time income tax exemption for two years in addition to the exemption provided for in the schedule attached hereto;

2/ An investor who has invested within an industrial parks shall be entitled, to a one time income tax exemption for two years in addition to the exemption provided for in the schedule attached hereto provided that he exports 80% or above of the product from his manufacturing industry or supplies as production input to an investor who exports his products.

**7. Replacement of the Income Tax Incentive**

The Council of Ministers may replace the income tax incentive provided under this Regulation by a new type of tax incentive system.

**8. Declaration of Income During Income Tax Exemption Period**

1/ An investor shall only be entitled to the exemptions specified under Articles 4, 5 and 6 of this Regulation if he submits to the relevant Tax Authority his books of account as provided under the Income Tax Proclamation;

፪/ ማንኛውም ባለሀብት የታክስ ማበረታቻ የሚያስገኙ ሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች የተሰማራ እንደሆነ ለታክስ ማበረታቻ ዓላማ የእያንዳንዱን ኢንቨስትመንት ገቢ ለየብቻ ማሳወቅ አለበት፤

፫/ የማበረታቻ ተጠቃሚ የሆነ ባለሀብት በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሒሳብ መዝገቡን ያላቀረበ እንደሆነ በገቢ ግብር አዋጅ ገቢን ስለአለማሳወቅ የተቀመጠው ቅጣትና ወለድ ተፈፃሚ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ግዴታውን ላልተወጣበት የግብር ዘመን የግብር እፎይታ ተጠቃሚ መሆኑ ቀሪ ይሆናል፤

፬/ ባለሀብቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገውን ግዴታው ያልተወጣው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በተመለከተ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፱. <u>ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ ስለሚጀምርበት ጊዜ</u>**

፩/ ከገቢ ግብር ነፃ የመሆኛ ዘመን መቆጠር የሚጀምረው አዲስ ኢንቨስትመንት ከሆነ ባለሀብቱ የንግድ ሥራ ፈቃድ ከወሰደበት ወይም ነባር ኢንቨስትመንት ከሆነ የማስፋፊያ ፈቃድ ከወሰደበት ቀን አንስቶ ይሆናል፤

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) አፈፃፀም አግባብ ያለው መሥሪያ ቤት ባለሀብቱ የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የማስፋፊያ ፈቃድ የወሰደበትን ቀን ለገቢዎች ሚኒስቴር ያሳውቃል፤

2/ If an investor is engaged in two or more investment activities to which he is entitled to tax incentives for the purpose of the tax incentive shall separately declare his income from each investment activity;

3/ If the beneficiary of the tax incentive fails to submit its books of account as provided in the Income Tax Proclamation, in addition to paying penalty and interest provided under the Income Tax Proclamation shall not be granted the tax holiday in the year it failed to fulfill its obligations;

4/ If the failure of the investor to fulfill its obligations under Sub-Article (1) of this Article is due to force majeure as defined by a Directive to be issued by the Ministry he shall not be subject to measures provided under Sub-Article (3) of this Article.

**9. <u>Commencement of Period of Income Tax Exemption</u>**

1/ The period of exemption from income tax under this Regulation shall begin from the date the investor obtained a business license or from the date the investor obtained expansion permit;

2/ For the purposes of Sub-Article (1) of this Article, the appropriate organ shall notify the Ministry of Revenue the date on which the business license or the expansion permit is issued to the investor;

፫/ ማንኛውም ባለሀብት ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ጀምሮ ግብር የከፈለ እንደሆነና ከዚህ በኋላ የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ መሆኑን የሚገልፅ ደብዳቤ ያመጣ እንደሆን የከፈለውን ግብር ተመላሽ መጠየቅ አይችልም፡፡

**፲. <u>ኪሣራን ስለማስተላለፍ</u>**

፩/ ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ በተሰጠበት ዘመን ውስጥ ኪሣራ ያጋጠመው ማንኛውም ባለሀብት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆኛ ዘመኑ ከተጠናቀቀ በኋላ የዚሁ ዘመን ግማሽ ለሚሆን ተከታታይ ጊዜ ኪሣራው ይተላለፍለታል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ኪሳራን የማስተላለፍ ዘመን ሲሰላ ግማሽ ዓመት ያጋጠመ እንደሆነ እንደሙሉ የገቢ ግብር ዘመን ይቆጠራል፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም ከገቢ ግብር ነፃ በመሆኛ ዘመን ኪሳራ የደረሰበት ማንኛውም ባለሀብት የደረሰበትን ኪሣራ ከአምስት የገቢ ግብር ዘመን በላይ ማስተላለፍ አይችልም፤

፬/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፪) በተጠቀሰው ተጨማሪ የማበረታቻ ጊዜ ውስጥ የሚያጋጥም ኪሳራ ኪሳራን በማስተላለፍ እንዲካካስ አይደረግም፡፡



3/ An investor shall not be entitled to a refund of the tax paid if he submits the tax incentive certificate after he has paid taxes on the production or rendition of services carried out before such date.

**10. <u>Loss Carry Forward</u>**

1/ An investor who has incurred loss within the period of income tax exemption shall be allowed to carry forward such loss for half of the income tax exemption period after the expiry of such period;

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, for the purpose of calculating the period of loss carry forward, a half-year period shall be considered as a full income tax period;

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) and (2) of this Article, an investor who has incurred loss during the income tax exemption period may not be allowed to carry forward such loss for more than five income tax period;

4/ Any loss incurred during the additional tax holiday period provided under Sub-Article (1) and (2) of Article 6 shall not be carried forward.

**፲፩. የግብር እፎይታ ተጠቃሚነት ላይ ስለሚጣል ገደብ**

የግብር እፎይታ የሚያስገኝ ኢንቨስትመንት ባለቤት የሆነ ሰው የተሠማራበትን ኢንቨስትመንት ዘግቶ ተመልሶ የእፎይታ ጊዜ በሚያሰጥ ኢንቨስትመንት ላይ ከተሰማራ ቢያንስ በዘጋው ኢንቨስትመንት የተጠቀመበትን የእፎይታ ጊዜ ለሚያክል ጊዜ የግብር እፎይታ ተጠቃሚ አይሆንም፡፡ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የመሆን ማበረታቻ

**፲፪. የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ስለመሆን**

፩/ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ከተዘረዘሩት የሥራ መስኮች በአንዱ የተሠማራ አዲስ ኢንቨስትመንት ወይም የነባር ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላል፤

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) አፈፃፀም ባለሀብቱ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈልጋቸውን የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ዝርዝር ወይም እንደአግባብነቱ ዝርዝሮቹን የሚያስረዳ ሰነድ እና ግንባታው የሚጠይቀውን ግብዓቶች ዓይነትና መጠን የሚያሳይ የፀደቀ የተፈላጊ ዕቃ ብዛት ሰነድ በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ ማስፈቀድ ይኖርበታል፤

**11. Limitation or Restriction on Entitlement to Tax Exemption**

Where an investor ceases to operate its investment and re-engages in another investment activity which qualifies for tax exemption shall not be entitled to a tax holiday for a period which he has already used for the closed business. The details shall be provided under a Directive to be issued by the Ministry.

## PART THREE

## CUSTOM DUTY INCENTIVES

**12. Exemption of Capital Goods and Construction Materials from Customs Duty**

1/ New investor or an investor expanding or upgrading existing investment engaged in one of the areas of investment specified in the Schedule attached hereto, may import duty free capital goods and construction materials necessary for the establishment of a new investment or the expansion or upgrading of an existing investment;

2/ For the implementation of Sub-Article (1) of this Article, the investor shall submit, the list of capital goods and approved construction materials or as appropriate document that explains the list or the bill of quantities of construction materials to be used as an input to be imported duty-free and get approval of same from the appropriate organ;

፫/ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆነ ባለሀብት ከሀገር ውስጥ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ወይም ከአስመጪ የካፒታል ወይም የግንባታ ዕቃዎችን ሲገዛ ዕቃዎቹን ለማምረት በግብዓትነት በዋሉት ጥሬ ዕቃዎች ወይም ግብዓቶች ላይ የተከፈለው የጉምሩክ ቀረጥ ተመላሽ ይደረጋል፤

፬/ በዚህ ደንብ መሠረት የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ የሚፈቀድለት ማንኛውም ባለሀብት ዋጋቸው ከካፒታል ዕቃዎቹ ጠቅላላ ዋጋ ፲፭ (አሥራ አምስት) በመቶ የማይበልጥ መለዋወጫ ዕቃዎች እንደሁኔታው የማበረታቻው ተጠቃሚ ለመሆን ብቁ ከሆነበት ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡ በማናቸውም ሁኔታ በዚህ አንቀጽ መሠረት የመለዋወጫ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት የሚቻለው በድምሩ ለአምስት ዓመታት ብቻ ነው፤

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ነባር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የተፈቀደው ማበረታቻ ተጠቃሚ ለመሆን ጥያቄ የሚያቀርብ ባለሀብት ሊያቀርባቸው የሚገቡ ማስረጃዎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

3/ If an investor entitled to a duty-free incentive buys capital goods or construction materials from local manufacturing industries, he shall be refunded with the import tax paid for the raw materials or components used as inputs for the production of such goods;

4/ An investor eligible to a duty-free incentive pursuant to this Article, shall be allowed to import spare parts the value of which is not greater than 15% of the total value of the capital goods within five years from the date he becomes eligible for the incentives or from the date the business license is issued, as the case may be. The period in which spare parts shall be imported free of duty as per this Regulation shall not in any way exceed a total of five years;

5/ Evidences that shall be submitted by an investor who applies to be a beneficiary of tax incentives provided under Sub-Article (1) of this Article for expansion or upgrading of existing investments shall be prescribed in a Directive to be issued by the Ministry.

**፲፫. የተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መሆን**

ለኢንቨስትመንት ዓላማ የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው የሚገቡበት ሁኔታ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ዓይነትና ባህሪ መሠረት በማድረግ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ሊፈቅድ የሚችለው ከፒክ አፕ እና ስቴሽን ዋገን ውጪ ያሉ ተሽከርካሪዎችን ነው፡፡

**፲፬. ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ የገባ ዕቃን ስለማስተላለፍ**

፩/ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ የገባ ማናቸውም የካፒታል ዕቃ ወይም የግንባታ ዕቃ ተመሳሳይ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብት ላለው ሰው ሊተላለፍ ይችላል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም አስቀድሞ ተገቢው የጉምሩክ ቀረጥ ተከፍሎ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ የገባ ማናቸውም የካፒታል ዕቃ ወይም የግንባታ ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ሰው ሊተላለፍ ይችላል፤

፫/ ባለሀብቱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ ያስገባውን የካፒታል ዕቃ ወይም የግንባታ ዕቃ መልሶ ከሀገር እንዲወጣ ማድረግ ይችላል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ሰው ሊተላለፍ የሚችለው የታክስ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ለማስተላለፍ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሲኖሩ ብቻ ይሆናል፤

**13. Exemption of Motor Vehicles from Customs Duties**

The total or partial exemptions from customs duties to be granted for motor vehicles used for investment purposes shall be determined by Directives to be issued by the Ministry based on the types and nature of investment projects. The exemption from customs duties to be granted by the Minister in accordance with this Article shall not include pickup and station wagon vehicles.

**14. Transfer of Duty Free Imported Goods**

1/ Capital goods or construction materials imported free of customs duty may be transferred to persons with similar duty-free privileges;

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the capital goods or construction materials imported free of customs duty may be transferred, up on effecting payment of the appropriate customs duty, to persons having no similar duty-free privileges;

3/ The investor may re-export the duty-free imported capital goods or construction materials;

4/ Transfer of goods imported duty free pursuant to Sub-Article (2) of this Article may only be made to a person who does not have duty-free privileges on conditions prescribed in a Directive to be issued by the Tax Authority which force the investor to transfer such property.

፭/ የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ባለሀብት አግባብ ባለው የጉምሩክ አዋጅ ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል፡፡

**፲፭. <u>በኢንቨስትመንት ቦርድ የተላለፈ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ውሳኔዎች</u>**

አዋጁ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በኢንቨስትመንት ቦርድ የተወሰኑ ነገር ግን በዚህ ደንብ ያልተካተቱ የገቢ ግብር እፎይታ እና የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻዎች ቀጣይነት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

**<u>ክፍል አራት</u>**

**<u>የማዕድን፣ነዳጅ እና የጂኦተርማል ሥራዎች</u>**

**፲፮. <u>ለማዕድን ኢንቨስትመንት የሚሰጥ ማበረታቻ</u>**

፩/ የማዕድን ሥራዎች

ሀ) ማንኛውም የምርመራ ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ለሥራው የሚያስፈልጉና በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው መሣሪያዎች፣ ማሽነሪዎች እና አላቂ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ይሆናሉ፤

ለ) ማንኛውም የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ለሥራው የሚያስፈልጉና በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው የማምረት ሥራውን ለመጀመር የሚያስችሉ

5/ Any investor who contravenes the provisions of this Article shall be punishable in accordance with the relevant provisions of the Customs Proclamation.

**15. <u>Decisions made by the Investment Board on Customs Duties and Taxes</u>**

The application of decisions of the Ethiopian Investment Board on tax holiday and customs duty privileges made before the entry into force of the Proclamation that are not included in this Regulation shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry.

**<u>PART FOUR</u>**

**<u>MINING, PETROLEUM AND GEOTHERMAL WORKS</u>**

**16. <u>Incentives for Mining Investment</u>**

1/ Mining

a) Any holder of an exploration license or his contractor may import into Ethiopia equipment, machinery and consumables that are required for its operations in accordance with the work program approved by the Regulatory Institution free from customs duties;

b) A small scale or large scale mining licensee or his contractor may import into Ethiopia equipment, machinery and consumables that are required to start the mining operation in accordance with the work

መሣሪያዎች፣ ማሽነሪዎች እና አላቂ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ይሆናሉ፤

ሐ) የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ የምርት ሥራውን በላቀ ደረጃ ለማስፋፋት ሲፈልግና የማስፋፊያው ዕቅድ በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ሲፀድቅ ለማስፋፊያ ሥራው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን፣ ማሽነሪዎችን እና አላቂ ዕቃዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላል፤

መ) የባህላዊ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ወይም አሸዋ ወይም ገረጋንቲ ለማምረት የሚያስችል ፈቃድ ያለው ማንኛውም የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ በዚህ ንዑስ-አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) የተመለከቱት የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብት ተጠቃሚ አይሆንም፤

ሠ) የማዕድን ምርመራ ሥራ ባለፈቃድ ለማዕድን ሥራው አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ለመሰብሰብ የሚያስፈልግ አውሮፕላን፣ ሄሊኮፕተር፣ ድሮን እና/ወይም ሌሎች ለሥራው አግባብነት ያላቸውን የመመርመሪያ መሣሪያዎች ከተቆጣጣሪው መስሪያ ቤት ድጋፍ ሲያገኝ ከቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፤

program approved by the Regulatory Institution free of customs duties;

c) The holder of a small scale or large scale mining license who wishes to embark on a major mine production expansion shall have the right to import free of customs duties, equipment, machinery and consumables needed for the expansion provided that the Regulatory Institution has approved the expansion program;

d) The holder of artisanal mining license or the holder of any construction minerals mining licensee issued for the mining of sand or selected materials shall not be entitled to exemptions from customs duties and taxes under paragraphs (a), (b) and (c) of this Sub-Article;

e) The holder of a mining license may import free from customs duties aircraft, helicopter, drone and/or other exploration equipment for the purpose of collecting relevant information for the mining activities after securing recommendations from the Regulatory Institution;

ረ) ማንኛውም ባለፈቃድ የተፈቀዱለትን መሣሪያዎች እና ማሽነሪዎች በማዕድን ማምረት ቅድመ ዝግጅት ጊዜ ማስገባት ካልቻለ ማዕድን ማምረት ከጀመረ በኋላ እስከ አምስት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት ይችላል፡፡

፪/ በማዕድን ዋጋ ላይ ተጨማሪ እሴት ማከል፡-

ሀ) ማንኛውም የመቅረፅ ዕደ ጥበብ ባለፈቃድ ወይም የማጣራት ባለፈቃድ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ የማዕድን ምርት የሚያመርት ከሆነ በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ለሥራው ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው መሣሪያዎች እና ማሽነሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ይሆናሉ፤

ለ) በዚህ ንዑስ-አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት መብት ፀንቶ የሚቆየው ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ለ፫ ዓመት ብቻ ይሆናል፤

፫/ የነዳጅ እና የጂኦተርማል ሥራዎች፡-

ሀ) ማንኛውም የምርመራ ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ለሥራው የሚያስፈልጉና በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው መሣሪያዎች፣ ማሽነሪዎች እና አላቂ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ይሆናሉ፤



f) The holder of a mining license who is unable to import equipment and machinery at pre-development stage may import such goods within five years from the commencement of production free of customs duties.

2/ Value Addition on Mining

a) The holder of a handicraft license or a refinery licensee who is engaged in the export of minerals may import equipment and machinery that are needed for its operations in accordance with the work program approved by the Regulatory Institution free from customs duties;

b) Notwithstanding the provisions of paragraph (a) of this Sub-Article the privilege to import goods free of customs duties shall remain valid only for three years from the date of issuance of the license;

3/ Petroleum and Geothermal Works

a) Any holder of an exploration license or his contractor may import into Ethiopia equipment, machinery and consumables that are required for its operations in accordance with the work program approved by the Regulatory Institution free from customs duties;

ለ) ማንኛውም የነዳጅ ወይም የጂኦተርማል ማምረት ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው የቁፋሮ፣ የጂኦሎጂካል፣ የጂኦፊዚካል፣ የማምረቻ፣ የማዘጋጃ፣ የማጣሪያ፣ ማጓጓዣ እና ሌሎች ለነዳጅ እና ጂኦተረማል ሥራዎች አስፈላጊ የሆኑ መሣሪዎችና ዕቃዎች የአየር፣ የባሕር መጓጓዣዎችን እና ሌሎች የመጓጓዣ መሣሪያዎችንና መለዋወጫቸውን ጨምሮ ለሥራው ማስፈሚያ የሚያስፈልገውን ነዳጅ፣ ኬሚካሎች፣ ዘይት፣ ቅባትና መለዋወጫዎች፣ ፊልሞች፣ ሳይዝሚክ ቴፖች፣ ተንቀሳቃሽ ቤቶች፣ ተንቀሳቃሽ ቢሮዎችና ተገጣጣሚ ስትራክቸሮች የተፈታቱ ክፍሎች እና ለነዳጅ ሥራ እና ጂኦተረማል አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ቁሳቁሶች ከጉምሩክ ቀረጥ ክፍያዎች ነፃ ይሆናሉ፤

ሐ) የውጭ ሀገር የሆኑ የነዳጅ ባለፈቃዱ ወይም የተቋራጩ ተቀጣሪ ሠራተኞች ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገቧቸው የቤት ዕቃዎችና የግል መገልገያዎች ፀንተው በሚሰራባቸው ሕጎች መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥ ክፍያዎች ነፃ ይሆናሉ፡፡

፬/ የባዮፊዩል ሥራዎች

ሀ) የባዮፊዩል ልማት ባለፈቃድ እንደፈቃዱ ዓይነት በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ለሥራው የሚያስፈልጉት ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው መሣሪያዎችና ማሽነሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ይሆናሉ፤

b) Any holder of Petroleum or Geothermal license or his contractor shall be entitled to import into Ethiopia all drilling, geological, geophysical, production, treating, processing, transportation and other machinery and equipment necessary in Petroleum and Geothermal Operations, including aircraft, vessels, and other transportation equipment and parts thereof. Fuels, chemicals, lubricants, films, seismic tapes, house trailers, disassembled prefabricated structures and other materials necessary for Petroleum and Geothermal Operations free of customs duties of any kind;

c) Expatriate employees of a Petroleum license holder or the contractor shall be entitled to import into Ethiopia household goods and personal effects free of customs duties, of any kind in accordance with prevailing Laws.

4/ Biofuel Works

a) Equipment and machinery imported by the holder of a biofuel license for its activities to be carried out based on the work program approved by the regulatory agency depending on the type of license shall be imported free of customs duties;

ለ) በዚህ ንዑስ-አንቀጽ ፊደል-ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የማስገባት መብት ፀንቶ የሚቆየው ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ለ፭ ዓመት ብቻ ይሆናል፤

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ የገባ ዕቃ ሚኒስቴሩ በቅድሚያ ሳይፈቅድና ተገቢው የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፈልበት አይተላለፍም፡፡ ሆኖም ተቆጣጣሪውን ባለስልጣን በቅድሚያ በማስፈቀድ ዕቃውን የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፈልበት መልሶ ከሀገር ማስወጣት ወይም ተመሳሳይ የቀረጥ ነፃ መብት ላለው ሰው ማስተላለፍ ይቻላል፤

፮/ ለዚህ የደንቡ ክፍል አፈፃፀም “አላቂ ዕቃ” ማለት ለማዕድን፣ ለነዳጅ እና ለጂኦተርማል ሥራዎች የሚያስፈልግ ኬሚካል፣ ድማሚት እና ሌሎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚዘረዝራቸው ዕቃዎች ናቸው፡፡

## ክፍል አምስት

## የታክስ ማበረታቻዎች አስተዳደር

### ፲፯. በግንባታ ዕቃዎች ላይ ስለሚደረግ ቁጥጥር

፩/ በዚህ ደንብ መሠረት የግንባታ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር እንዲያስገባ የተፈቀደለት ባለሀብት የግንባታ ዕቃዎቹ ለታለመው ዓላማ የዋሉ መሆኑን የሚያስረዳ የግንባታ ፈቃድ በሰጠው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተረጋገጠ ማስረጃ በየሦስት ወሩ ማቅረብ አለበት፤

b) Notwithstanding the provisions of paragraph (a) of this Sub-Article the privilege to import goods free of customs duties shall remain valid only for 5 years from the date of issuance of the license;

5/ Any item imported free of customs duties and taxes into Ethiopia pursuant to the provisions of this Article may not be transferred without having obtained permission from the Ministry and paid the required duties; provided however, that such item may be re-exported free of customs duties or transferred to persons with similar duty free privileges upon the permission of the Regulatory Institution;

6/ For purposes of this Part of the Regulation "Consumables" mean chemicals, dynamite and other materials to be used for mining, petroleum and geothermal activities specified in a Directive to be issued by the Ministry.

## PART FIVE

## ADMINISTRATION OF TAX INCENTIVES

### 17. Control on Building Materials

1/ An investor who is entitled to import building materials free of customs duties and taxes in accordance with this Regulation shall submit every quarter evidence, approved by Government office assigned to give construction permit, which shows that the materials are used for intended purposes;

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ለኢንዱስትሪ ፓርክ ግንባታ ተፈፃሚ አይሆንም፤

፫/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ሊቀርቡ የሚገባቸውን ማስረጃዎች ዓይነት እና ለማን ማቅረብ እንዳለበት በመመሪያ ይወስናል፡፡

**፲፰. የተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች የወል ተግባራት እና ኃላፊነት**

ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች:-

፩/ ባለሀብቱ የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ መሆን እንዲችል ለሚኒስቴሩ የሚከተለውን ማረጋገጫ ይሰጣሉ፡-

ሀ) ባለሀብቱ የንግድ ፈቃድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ ስለመሆኑ፤

ለ) ባለሀብቱ ምርት ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት የጀመረበትን ጊዜ፤

፪/ በዚህ ደንብ መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የመሆን ማበረታቻ የሚፈቀድለት ባለሀብት ወደ ሀገር ሊያስገባቸው የሚችሉ ለኢንቨስትመንቱ አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች ዝርዝር እና ትክክለኛ እና ወቅታዊ ዋጋቸው በሚመለከት ለሚኒስቴሩ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባሉ፤

፫/ ለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ብቁ የሚሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች ለመምረጫ የሚያገለግሉ መስፈርቶች በሚዘጋጁበት ጊዜ ይሳተፋሉ፤

፬/ ማንኛውንም ባለሀብት ከቀረጥ ነፃ ሆኖ ወደ ሀገር ያስገባውን ዕቃ ዋጋው እና ቀሪ የተደረገውን ቀረጥ መጠን የሚያሳይ ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴሩ ያቀርባሉ፤

2/ The provision of Sub-Article (1) of this Article shall not apply to construction of Industrial Parks;

3/ The Ministry shall by a Directive prescribe the type of evidence and for whom that are required to be submitted in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

**18. Common Duties and Responsibilities of Regulatory Institutions**

The Regulatory Institutions shall:

1/ ascertain the following to the Ministry to enable the investor to be eligible for tax holiday privilege:

a) that the investor has obtained business license and started operations;

b) the date on which the investor started production or rendition of services;

2/ submit a proposal, to the Ministry, regarding the list and their exact and current market prices of equipment, that may be allowed to be imported by Investors that are required for its operation free of duties and taxes in accordance with this Regulation;

3/ participate in setting standards or eligibility criteria for entitlement of tax incentive.

4/ submit to the Ministry quarterly reports that show the items imported free of duties and taxes and the amount of duties and taxes forgone with respect to each investment;

፭/ ለባለሀብቱ የተሰጠውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ እና የተገኘውን ጥቅም በተለይም የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በማሳደግ ረገድ እያንዳንዱ ባለሀብት ለሀገሪቱ ያስገኘውን ጥቅም የሚያሳይ ሪፖርት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባሉ፡፡

## ፲፱. <u>የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተግባራት እና ኃላፊነት</u>

የዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፰ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣቸው ባለሀብቶች በዚህ ደንብ መሠረት፡-

ሀ) ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የመሆን ማበረታቻ ለማግኘት በተዘረጋው ሥርዓት አማካኝነት የሚያቀርቡትን ማመልከቻ ይቀበላል፣ የማበረታቻ ጥያቄው ሚኒስቴሩ ካወጣው መመሪያ ጋር የተጣጣመ መሆኑን በመመርመር ያረጋግጣል፣ ከድጋፍ ጋር ለውሳኔ ለሚኒስቴሩ ያስተላልፋል፤

ለ) የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ ለመሆን በተዘረጋው ሥርዓት አማካኝነት የሚያቀርቡትን ማመልከቻ ይቀበላል፣ የማበረታቻ ጥያቄው ሚኒስቴሩ ካወጣው መመሪያ ጋር የተጣጣመ መሆኑን በመመርመር ያረጋግጣል፣ ከድጋፍ ደብዳቤ ጋር ለውሳኔ ለሚኒስቴሩ ያስተላልፋል፤

5/ carry out annual evaluations on the benefits that each investment has brought in terms of creating employment opportunity and earning foreign currency and report the same to the Ministry not later than three months after the end of the fiscal year.

## 19. <u>Duties and Responsibilities of the Ethiopian Investment Commission</u>

Without prejudice to the provisions of Article 18 of this Regulation, the Ethiopian Investment Commission shall have the following duties and responsibilities:

1/ In accordance with this Regulation:

a) accept applications for duty free privilege from investors who have acquired investment license through the system developed; verify whether the request for incentives is consistent with the Directive issued by the Ministry, transfer the application with its recommendation for approval by the Ministry;

b) accept applications for tax holiday from investors who have acquired investment license through the system developed, verify whether the request for incentives is consistent with the Directive issued by the Ministry, transfer the application with its recommendation for apprpval by the Ministry;

፪/ አግባብነት ባለው ሕግ እና መመሪያ መሠረት የካፒታል እና የግንባታ ዕቃዎችን እና መለዋወጫዎችን ከቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር እንዲያስገባ የተፈቀደለት ባለሀብት ዕቃዎቹን ለታለመላቸው ዓላማ ያዋለ መሆኑን ለመቆጣጠር በመስክ ምልከታ፣ በሪፖርት፣ ተቆጣጣሪ በመመደብ ወይም በሌላ ማናቸውም ዘዴ ተከታታይነት ያለው ክትትል ያካሂዳል፣ በየዓመቱም ለሚኒስቴሩ የተጠቃለለ የአፈፃፀም ሪፖርት ይልካል፡፡

፳. <u>የሌሎች ኢንቨስትመንትን የማስፋፋት ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ተግባራት እና ኃላፊነት</u>

ኢንቨስትመንትን የማስፋፋት ኃላፊነት የተሰጣቸው የፌደራል እና የክልል አካላት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፱ ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተሰጠው ተግባራት እና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡

፳፩. <u>የገቢዎች ሚኒስቴር ተግባራት እና ኃላፊነት</u>

የገቢዎች ሚኒስቴር፡-

፩/ የተፈቀደው የገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ ሚኒስቴሩ ካወጣው መመሪያ ጋር የተጣጣመ መሆኑን በመመርመር የገቢ ግብር ነፃ መብቱን ተፈፃሚ ያደርጋል፤

፪/ ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ የተሰጣቸውን ባለሀብቶች ዝርዝር፣ የተሰጣቸውን ከግብር ነፃ የመሆን ጊዜ ርዝመት እና የሚያበቃበትን ጊዜ የሚያሳይ መዝገብ ይይዛል፤

፫/ በዚህ ደንብ መሠረት በተሰጠው ከግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ ምክንያት የታጣውን የገቢ ግብር የሚያሳይ መዝገብ ይይዛል፤



2/ Through field inspections, reports, by assigning supervisors or through any other means ascertain that the investor granted duty free privileges to import capital goods, building materials and spare parts in accordance with the relevant laws and Directive have used such goods for the designated purposes; and submit annual consolidated reports to the Ministry.

20. <u>Duties and Responsibilities of other Organs with a Mandate to Encourage Investment</u>

Federal and Regional Government Organs with a mandate to encourage investment shall have the same duties and responsibilities granted to the Ethiopian Investment Commission under Article 19 of this Regulation.

21. <u>Duties and Responsibilities of the Ministry of Revenue</u>

The Ministry of Revenue shall:

1/ implement the tax holiday incentive after ascertaining that it is consistent with the Directive issued by the Ministry;

2/ maintain a record that shows list of investors which are granted income tax exemption, the length of period of such exemption and the time the tax holiday ends;

3/ maintain a record that shows the income tax forgone due to the favorable deviation from the income tax law under this Regulation;

፬/ ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት የተሰጣቸውን ባለሀብቶች ዝርዝር፣ የተሰማሩበትን የኢንቨስትመንት መስክ እና ለባለሀብቶች በተሰጠው ከግብር ነፃ የመሆን መብት ምክንያት የታጣውን ገቢ እና ሌሎች መረጃዎችን የሚያሳይ ሪፖርት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

## ፳፪. የጉምሩክ ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባራት

የጉምሩክ ኮሚሽን፡-

፩/ የተፈቀደው ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የመሆን ማበረታቻ ሚኒስቴሩ ካወጣው መመሪያ ጋር የተጣጣመ መሆኑን በመመርመር ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ ሆነው ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል፤

፪/ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የመሆን ማበረታቻ የተፈቀደላቸውን ባለሀብቶች ዝርዝር፣ የተሠማሩበትን የኢንቨስትመንት መስክ እና ከቀረጥ ነፃ ሆነው ወደ ሀገር የገቡትን ዕቃዎች ዋጋ እና የታጣውን ገቢ የሚያሳይ መዝገብ ይይዛል፤

፫/ ባለሀብቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር ያስገቧቸው ዕቃዎች ለታለመላቸው ዓላማ የዋሉ መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችል የድህረ ኦዲት ተግባር ያከናውናል፤

፬/ ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ወደ ሀገር ያስገቧቸውን ዕቃዎች ለታለመለት ዓላማ ያላዋሉ መሆኑ በኦዲት ሲረጋገጥ ፀንተው በሚሠራባቸው ሕጐች መሠረት ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤

4/ submit annual report to the Ministry within two months after the end of the fiscal year which, among others, shows the list of investors, the area of investment and the amount of tax forgone as well as other information.

## 22. Duties and Responsibilities of Customs Commission

The Customs Commission shall:

1/ allow goods to enter into Ethiopia free of taxes and duties after ascertaining that the tax incentive is consistent with the Directive issued by the Ministry;

2/ maintain a record that shows the list of investors which are granted custom duties exemption, the area of investment, the price of items they have imported free of customs duties and the tax forgone;

3/ carry out post audit to ascertain that items imported by the investor free of taxes and duties are used for intended purposes;

4/ take legal measures in accordance with applicable laws if proved through post audit that the investor have used goods imported under incentive scheme for unintended purposes;

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተከናወኑ ተግባራትን የሚያሳይ የሩብ ዓመት ሪፖርት የሩብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በ፲ ቀናት ጊዜ እንዲሁም ዓመታዊ ሪፖርት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

## ፳፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ተግባራት እና ኃላፊነት</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር፡-

፩/ በዚህ ደንብ መሠረት ለማበረታቻ ብቁ ለሆነ ኢንቨስትመንት ከገቢ ግብር ወይም ቀረጥ ነፃ የመሆን መብት የሚያስገኝ የታክስ ማበረታቻ ይሰጣል፤

፪/ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለማግኘት የብቃት መመዘኛ መስፈርቶችን፣ ከቀረጥ ነፃ ሆነው ወደ ሀገር ሊገቡ ወይም ከሀገር ውስጥ ሊገዙ የሚችሉ ዕቃዎችን ዝርዝር፣ የእነዚህ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ለመሆን ጥያቄ የሚያቀርቡ ባለሀብቶች ሊያቀርቧቸው የሚገባ ሰነዶችን የሚያሳይ መመሪያ ያወጣል፤

፫/ እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለታለመለት ዓላማ የዋለ መሆኑን በማረጋገጥ ረገድ ያከናወነውን ተግባር በመደበኛ ሁኔታ ይቆጣጠራል፤

፬/ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በመስጠቱ ምክንያት የታጣውን ገቢ ያጠቃልላል፣ የተጠቃለለውን ሒሣብ እና የኢንቨስትመንት ማበረታቻው በመሰጠቱ ምክንያት የተገኘውን ጥቅም የሚያሳይ ሪፖርት በዓመታዊ የመንግሥት የሒሣብ ሪፖርት ውስጥ በማካተት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ በየዓመቱ ይህንን ሪፖርት አትሞ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፤



5/ submit to the Ministry quarterly report within 10 days after the end of each quarter and annual report within one month after the end of each fiscal year on activities carried out in accordance with this Article.

## 23. <u>Duties and Responsibilities of the Ministry of Finance</u>

The Ministry of Finance shall:

1/ grant tax incentives to investments eligible under this Regulation which entitles them to tax or duty exemption;

2/ issue a Directive on the eligibility criteria for tax incentives, the list of items that can be allowed to be imported free of duties and taxes or purchased locally, and the documentation that shall be provided to be entitled for such privileges;

3/ monitor on a regular basis the performance of each Regulatory Institution with respect to ensuring that tax incentives are used for designated purposes;

4/ consolidate the forgone revenue and report the tax forgone and the benefit acquired by granting such privileges to the House of Peoples' Representatives with its annual financial report and publish same annually;

፭/ የተፈቀደውን የቀረጥ እና ግብር ማበረታቻ መተንተን እና መቆጣጠር የሚያስችል የመረጃ ቋት ያደራጃል፤

፮/ የተሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን ለመቆጣጠር እና ግልጽ ለማድረግ የሚያስችል በዘርፍ እና በኢንዱስትሪ ደረጃ የሚከተሉትን መረጃዎች ይይዛል፡-

ሀ) ለተመዘገቡ ባለሀብቶች የተሰጠውን የቀረጥ እና የግብር ማበረታቻ፤

ለ) ለቀጣይ የበጀት ዓመት ባለሀብቶች ሊያቀርቡ ይችላሉ ተብሎ የሚገመተውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ጥያቄ፤

ሐ) በተያዘው የበጀት ዓመት ሊፈቀድ ይችላል ተብሎ በዕቅድ የተያዘውን የቀረጥ እና የግብር ማበረታቻ፤

መ) ለቀጣይ የበጀት ዓመት ሊፈቀድ ይችላል ተብሎ የታቀደውን የቀረጥ እና የግብር ማበረታቻ፤

፯/ የታክስ ማበረታቻ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረውን ውጤት ለማወቅ እንዲቻል የተሰጠውን ማበረታቻ እና በማበረታቻው ምክንያት የተገኘውን ጥቅም የሚያሳይ ትንታኔ ያከናውናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳፬. የታክስ ማበረታቻን ቀሪ ስለማድረግ

፩/ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የተሰረዘበት ባለሀብት የወሰደውን የታክስ ማበረታቻ እንዲመልስ ይደረጋል፤

5/ maintain a database for monitoring and analysis of tax incentives granted;

6/ for purposes of monitoring and transparency, shall maintain the aggregate data on a sectoral and per industry basis of:

a) the amount of tax incentives availed for registered investors;

b) the estimate claims of tax incentives immediately preceding the current year;

c) the programmed tax incentives for the current year;

d) the projected tax incentives for the following year;

7/ shall conduct cost-benefit analysis on the investment incentives to determine the impact of tax incentives on the economy of the country.

## PART SIX

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 24. Revocation of Tax Incentives

1/ An Investor whose investment license is revoked shall return all investment incentives acquired;

፪/ ያለአግባብ የተወሰዱ የታክስ ማበረታቻዎች የሚመለሱበት ሁኔታ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፳፭. ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነትን ባለመወጣት ስለሚጣል መቀጫ**

፩/ ማናቸውም የመንግሥት ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ በቂ ምክንያት ሳይኖረው በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት ስለታክስ ማበረታቻዎች አፈፃፀም ሊያቀርብ የሚገባውን ሪፖርት ወይም መረጃ ያላቀረበ እንደሆነ ፀንተው በሚሠሩባቸው ሕጎች መሠረት በወንጀል ወይም በአስተዳደር የሚኖርበት ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ እስከ ፫ (ሶስት) ወር የሚደርስ ደመወዝ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፣

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተጣለውን የገንዘብ መቀጫ የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፳፮. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ሚኒስቴሩ ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የሚያግዙ መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፯. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

፩/ ሚኒስቴሩ በዚህ ደንብ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መመሪያዎች እስከሚያወጣ ድረስ ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት በተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤቶች የወጡ መመሪያዎች ተፈፃሚነት ይቀጥላል፡፡

፪/ በተሻረው የኢንቨስትመንት ማበረታቻና ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸/፪ሺ፭ መሠረት የተሰጡ ማበረታቻዎች ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

2/ The Ministry shall determine, in a Directive, the manner of return of investment incentives improperly acquired.

**25. Penalty due to Failure to Submit Report**

1/ Without prejudice to the criminal or administrative responsibilities under the laws that are currently in force, any government official or employee who, without good cause, fail to report on the tax incentive performance as provided by this Regulation shall be subject to a fine of up to 3 (three) months of his salary;

2/ The Ministry is authorized to impose and collect the fine provided under Sub-Article (1) of this Article.

**26. Power to Issue Directives**

The Ministry may issue Directives necessary for the implementation of this Regulation.

**27. Transitional Provisions**

1/ Directives issued by Regulatory Institutions prior to the enactment of this Regulation shall remain in force until replaced by a new Directive to be issued by the Ministry by the power vested in him under this Regulation.

2/ Tax Incentives granted pursuant to the Investment Incentives and Investment Areas Reserved for Domestic Investors Council of Ministers Regulation No. 270/2012 (as amended) shall remain valid.

**፳፰. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

፩/ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸/፪ሺ፲፪ (እንደተሻሻለ) የኢንቨስመንት ማበረታቻዎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡፡

፪/ ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ ደንብ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፱. <u>ደንቡ የሚፀናበት ቀን</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፭ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ/ም**

**ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**28. <u>Repealed and Inapplicable laws</u>**

1/ Tax Incentives provided under the Investment Incentives and Investment Areas Reserved for Domestic Investors Council of Ministers Regulation No. 270/2012 (as amended) are hereby repealed.

2/ No Regulation, Directive or practice shall, in so far as they are inconsistent with this Regulation, be applicable with respect to matters provided for in this Regulation.

**29. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force up on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this day of 12th July, 2022.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## የኢንቨስትመንት መስኮች እና የገቢ ግብር ማበረታቻዎች ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|---|
| 1 | 1.1 የምግብ ኢንዱስትሪ | | |
| | 1.1.1 ሥጋና የሥጋ ውጤቶች ማቀነባበርና መጠበቅ | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.1.2 ዓሣና የዓሣ ውጤቶችን ማቀነባበር | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.1.3 አትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበርና መጠበቅ | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.1.4 የምግብ ዘይት ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.1.5 ወተት ማቀነባበር እና/ወይም የወተት ውጤቶችን ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.1.6 የምግብ ማሻሻያ፣ ተጨማሪዎች ወይም ንጥረ ነገሮች ወይም ስታርችና የስታርች ውጤቶችን ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.1.7 የእህል ምርት ውጤቶችን ማቀነባበር (ዱቄት ማምረትን ሳይጨምር) | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.1.8 ስኳር ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.1.9 ማካሮኒ፣ ፓስታ እና/ወይም የመሳሰሉ ምግቦችን ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.1.10 አዮዲን የተጨመረበት ጨው ማምረት | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.1.11 ሰው ሰራሽ ማር ማምረት | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.1.12 ተቆልቶ የተፈጨ ቡና፣ የሚሟሟ ቡና፣ ሻይ ማምረት | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.1.13 የእንስሳት መኖ ማቀነባበር | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

INVESTMENT AREAS AND INCOME TAX INCENTIVES SCHEDULE

| Item No. | Investment Area | Addis Ababa and Oromia Special Zone surrounding Addis Ababa | Other Areas |
|---|---|---|---|
| 1 | **1.1 Food Industry** | | |
| | 1.1.1 Processing and Preserving of Meat and Meat Products | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.1.2 Processing of Fish and Fish Products | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.1.3 Processing and Preserving vegetables and Fruits | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.1.4 Manufacturing of Edible oil | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.1.5 Processing of Milk and/or manufacturing of dairy products | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.1.6 Manufacture of food supplements, additions or substances or starches and starch products | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.1.7 Processing of grain products (excluding production of flour) | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.1.8 Manufacture of sugar | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 6 years |
| | 1.1.9 Manufacture of Macaroni, Pasta and/or other similar food items | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.1.10 Manufacture of iodized salt | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 1.1.11 Manufacture of artificial honey | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 1.1.12 Manufacture of roasted and grinded coffee, instant coffee and tea; | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 1.1.13 Processing of animal feed | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 4 years |

| ተ.ቁ | የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|---|
| | **1.2 የመጠጥ ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.2.1 የአልኮል መጠጥ ማምረት | ለ 1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.2.2 የወይን ጠጅ ማምረቻ | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.2.3 ቢራ እና/ወይም የቢራ ብቅል ማምረት | ለ 2 ዓመት ከገቢ ብር ነፃ የመሆን | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.2.4 የማዕድን ወይም የታሸጉ ሌሎች ውሃዎችን ማምረት | ለ 1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1..2.5 ለስላሳ መጠጥ ማምረት | ለ 1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | **1.3 የጨርቃ ጨርቅና የስፌት ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.3.1 የተለያዩ የጨርቃጨርቅ ጭረቶችን ማዘጋጀት፣ መፍተል፣ መሸመን፣ ማጠናቀቅ እና/ወይም ማተም (አልባሳትን ሳይጨምር) | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.3.2 ጣቃ ጨርቅ፣ ክር፣ ድርና ማግ፣ አልባሳትና ሌሎች የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶችን በማንጣት፣ በማቅለም፣ በማኮማተር፣ በማፍካት፣ በማጠንከር፣ ወርድንና ቁመትን በመጠበቅ ወይም በማስዋብ ማጠናቀቅ | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.3.3 ከአልባሳት በስተቀር የተዘጋጁ ጨርቃ ጨርቆችን ወይም ሹራብ ወይም ፎጣ ወይም ምንጣፍ ማምረት | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.3.4 የጨርቃ ጨርቅ አልባሳትን (የስፖርት አልባሳትን ጨምሮ) ወይም ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | **1.4 የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.4.1 ቆዳና ሌጦ ማለስለስና ማጠናቀቅ (ካለቀለት ደረጃ በታች ቆዳና ሌጦ ማልፋትን አይጨምርም) | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.4.2 ካለቀለት ደረጃ በታች ቆዳና ሌጦ ማልፋት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |

| Item No. | Investment Area | Addis Ababa and Oromia Special Zone surrounding Addis Ababa | Other Areas |
|---|---|---|---|
| | **1.2 Beverage Industry** | | |
| | 1.2.1 Manufacture of alcoholic beverages | Exemption from Income Tax for 1 year | Exemption from Income Tax for 2 years |
| | 1.2.2 Manufacture of wines | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 1.2.3 Manufacture of Beer and/or beer Malt | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 3 years |
| | 1.2.4 Manufacture of mineral water or other bottled water | Exemption from Income Tax for 1 year | Exemption from Income Tax for 2 years |
| | 1..2.5 Manufacture of soft drinks | Exemption from Income Tax for 1 year | Exemption from Income Tax for 2 years |
| | **1.3 Textile and Textile Products Industry** | | |
| | 1.3.1 Manufacture of different made-up textile articles, fibres, spinning, knitting and finishing (excluding apparels) | Exemption from Income Tax for 5 years | Exemption from Income Tax for 6 years |
| | 1.3.2 Finishing of fabrics, yarn, warp and weft, apparel and other textile products by bleaching, dyeing, shrinking, sanforizing, mercerizing or dressing | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 3 years |
| | 1.3.3 Manufacture of made-up textile articles or sweaters or towels or carpets except apparels | Exemption from Income Tax for 4 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.3.4 Manufacture of textile apparels (including sportswear) and other accessories | Exemption from Income Tax for 5 years | Exemption from Income Tax for 6 years |
| | **1.4 Leather and Leather Products Industry** | | |
| | 1.4.1 Tanning of hides and skins up to finished levels (excluding tanning of hides and skins below finished levels) | Exemption from Income Tax for 5 years | Exemption from Income Tax for 6 years |
| | 1.4.2 Tanning of hides and skins below finished level | No Income Tax Exemption | No Income Tax Exemption |

| ተ.ቁ | የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|---|
| | 1.4.3 የቆዳ ውጤቶች እና/ወይም ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.4.4 የቆዳ ወይም የቆዳ ምትክ ጫማ ማምረት | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | **1.5 የእንጨት ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.5.1 የእንጨት ውጤቶችን (እንጨት መሰንጠቅን፣ ጣውላ ማምረትን እና ቀድመው የተዘጋጁ የእንጨት ውጤቶችን መገጣጠምን ሳይጨምር) ማምረት | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | **1.6 የወረቀትና የወረቀት ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.6.1 ፐልፕ እና/ወይም ወረቀት ማምረት | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.6.2 የወረቀት ውጤቶችን ማምረት | ለ 1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | **1.7 የማተሚያ ኢንዱስትሪ** | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| | **1.8 የኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.8.1 መሠረታዊ ኬሚካሎችን (ኢታኖልን እና/ወይም ሰው ሰራሽ ጭረቶችን ጨምሮ)፣ እና/ወይም ሃይድሮጂን እና አሞኒያ ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.8.2 ማዳበሪያ እና/ወይም የናይትሮጅን ውህዶችን ማምረት | ለ 5 ዓመት ገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.8.3 መሠረታዊ (የመጀመሪያ ደረጃ) ፕላስቲኮችን እና/ወይም ሲንቴቲክ (ሰው ሰራሽ) ጎማ ጥሬ ዕቃዎችንና ጎማ ውጤቶችን ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.8.4 ጸረ-ተባይና የግብርና ኬሚካሎችን ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.8.5 ቀለም፣ ቫርኒሽ እና ተመሳሳይ ምርቶች፣ ማጣበቂያ እና/ወይም መሠረታዊ ያልሆኑ ኬሚካሎችን ማምረት | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

| Item No. | Investment Area | Addis Ababa and Oromia Special Zone surrounding Addis Ababa | Other Areas |
|---|---|---|---|
| | 1.4.3 Manufacture of Leather products and/or accessories | Exemption from Income Tax for 5 years | Exemption from Income Tax for 6 years |
| | 1.4.4 Manufacture of shoes from leather or substitutes of leather | Exemption from Income Tax for 5 years | Exemption from Income Tax for 6 years |
| | **1.5 Wood Products Industry** | | |
| | 1.5.1 Manufacture of Wood Products (excluding saw milling, timber making and assembling of semi-finished wood products) | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 3 years |
| | **1.6 Paper and Paper Products Industry** | | |
| | 1.6.1 Manufacture of Pulp and/or Paper | Exemption from Income Tax for 5 years | Exemption from Income Tax for 6 years |
| | 1.6.2 Manufacture of Paper products | Exemption from Income Tax for 1 year | Exemption from Income Tax for 2 years |
| | **1.7 Printing Industry** | No Income Tax Exemption | No Income Tax Exemption |
| | **1.8 Chemical and Chemical Products Industry** | | |
| | 1.8.1 Manufacture of basic chemicals (including ethanol and/or artificial fibers) and/ or green hydrogen and green ammonia | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 1.8.2 Manufacture of Fertilizers and/or nitrogen compounds | Exemption from Income Tax for 5 years | Exemption from Income Tax for 6 years |
| | 1.8.3 Manufacture of plastics and /or synthetic rubber raw materials in primary forms and rubber products | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.8.4 Manufacture of Pesticides and agricultural chemicals | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.8.5 Manufacture of paints, varnishes or similar coatings and/or non-basic chemicals | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 4 years |

| ተ.ቁ | የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|---|
| | 1.8.6 የንፅህናና የኮስሞቲክስ ዕቃዎች እና ግብዓቶች መፈብረክ | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | **1.9 የመሠረታዊ መድኃኒት ምርት እና የመድኃኒት ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.9.1 ለመድኃኒት ግብዓትነት የሚውሉ መሠረታዊ የመድኃኒት ውጤቶችን ማምረት | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.9.2 ለሰው አገልግሎት የሚውል መድኃኒት ማምረት (ክትባት ማምረትን ጨምሮ) | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.9.3 ለእንስሳት አገልግሎት የሚውል መድኃኒት ማምረት (ክትባት ማምረትን ጨምሮ) | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.9.4 ከመድኃኒት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን የማሸጊያ ምርቶች ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.9.5 የመድኃኒት ማሸግ ሥራዎች | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | **1.10 የፕላስቲክ ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.10.1 ፊስታልን ሳይጨምር የፕላስቲክ ውጤቶችን ማምረት | ለ 1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | **1.11 ብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.11.1 መስታወት እና/ወይም የመስታወት ወይም የሴራሚክ ውጤቶችን ማምረት | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.11.2 ሲሚንቶ ማምረት | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.11.3 የሸክላና የሲሚንቶ ውጤቶች ማምረት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| | 1.11.4 የካባ ድንጋዮችን ማውጣት ሳይጨምር የድንጋይ ውጤቶችን፣ ዕብነ በረድ እና ግራናይት የኖራ ድንጋይ መቁረጥ፣ ቅርፅ ማውጣት እና ማጠናቀቅ | ለ 1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.11.5 ኖራ ፣ ጀሶ እና/ወይም የመሳሰሉ መለሰኛዎችን ማምረት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

| Item No. | Investment Area | Addis Ababa and Oromia Special Zone surrounding Addis Ababa | Other Areas |
|---|---|---|---|
| | 1.8.6 Manufacture of sanitary and cosmetics products and inputs | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | **1.9 Basic Pharmaceutical Products and Pharmaceutical Preparations Industry** | | |
| | 1.9.1 Manufacture of inputs of basic pharmaceutical preparations | Exemption from Income Tax for 5 years | Exemption from Income Tax for 6 years |
| | 1.9.2 Manufacture of human medicines ( including vaccines) | Exemption from Income Tax.for 4 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.9.3 Manufacture of animal medicines( including vaccines) | Exemption from Income Tax for 4 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.9.4 Manufacture of Primary Packaging Materials | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.9.5 Packaging of Medicines | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 3 years |
| | **1.10 Plastic Products Industry** | | |
| | 1.10.1 Manufacture of plastic products excluding plastic bags | Exemption from Income Tax for 1 year | Exemption from Income Tax for 2 years |
| | **1.11 Other Non-Metallic Mineral Products Industry** | | |
| | 1.11.1 Manufacture of Glass and/or glass of ceramic products | Exemption from Income Tax for 4 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.11.2 Manufacture of Cement | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 1.11.3 Manufacture of clay and cement products | No Income Tax Exemption | No Income Tax Exemption |
| | 1.11.4 Cutting, shaping and finishing of stone products, marble and limestone excluding quarrying | Exemption from Income Tax for 1 year | Exemption from Income Tax for 2 years |
| | 1.11.5 Manufacture of lime, gypsum and/or similar coatings | No Income Tax Exemption | Exemption from Income Tax for 2 years |

| ተ.ቁ | የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|---|
| | **1.12 የመሠረታዊ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ /የማዕድን ማውጣትን ሳይጨምር/** | | |
| | 1.12.1 ብረት ፣የአረብ ብረት እና የብረት ማዕድናት ውጤቶችን መፈብረክ | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.12.2 መሠረታዊ የከበሩና የብረት ይዘት የሌላቸው ብረታ ብረቶችን ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.12.3 ከብረት እና ማግኔታዊ ያልሆኑ ብረታ ብረቶች ማቅለጥ/ማድለብና የተለያዩ ቅርፃችን ማውጣት | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | **1.13 ለስትራክቸር የሚያገለግሉ የብረታ ብረት ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.13.1 የማዋቀሪያ እና የተለያዩ የብረታ ብረት ውጤቶችን ማምረት (የቤት ክዳን ቆርቆሮንና ሚስማርን ሳይጨምር) | ለ 1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | **1.14 የኮምፒዩተር፣ የኤሌክትሮኒክስ እና የዕይታ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.14.1 ኮምፒዩተር እና ተጓዳኝ ዕቃዎችን እና/ወይም የኤሌክትሮኒክስ አካሎችንና ሰሌዳዎችን ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.14.2 የመገናኛ መሣሪያዎችን ወይም የፍጆታ ኤሌክትሮኒክስ/ቴሌቪዥን፣ ዲቪዲ፣ ሬዲዮ እና የመሳሰሉት/ዕቃዎችን ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.14.3 የመለኪያ፣ የመፈተሻ፣ የመቃኛ፣ የመቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን ወይም ሰዓት ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.14.4 የህክምና መሳሪያዎችን ወይም አቅርቦቶችን ማምረት | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.14.5 የህክምና መሳሪያዎችን መገጣጠም | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.14.6 የዕይታ ወይም የፎቶ ማንሻ ወይም መግነጢሳዊ እና የዕይታ ሚዲያ ዕቃዎችን ማምረት | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

| Item No. | Investment Area | Addis Ababa and Oromia Special Zone surrounding Addis Ababa | Other Areas |
|---|---|---|---|
| | **1.12 Basic Metals Industry (excluding mining of the minerals)** | | |
| | 1.12.1 Manufacture of iron, steel and iron products | Exemption from Income Tax for 5 years | Exemption from Income Tax for 6 years |
| | 1.12.2 Manufacture of basic precious and other non-ferrous metals | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 1.12.3 casting of iron and non-magnetic metals and produce such items in different shapes | Exemption from Income Tax for 4 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | **1.13 Structural Metal Products Industry** | | |
| | 1.13.1 Manufacture structural and different metal products (except corrugated metal sheets for roofing and nails) | Exemption from Income Tax for 1 year | Exemption from Income Tax for 2 years |
| | **1.14 Computer, Electronic and Optical Products Industry** | | |
| | 1.14.1 Manufacture of computers and accessories and/or electronic components and boards | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 1.14.2 Manufacture of communication equipment or consumer electronics (television, DVD, radio and similar items) | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 1.14.3 Manufacture of measuring, testing, surveying, controlling equipment and watches | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 1.14.4 Manufacture of medical equipment and supplies | Exemption from Income Tax for 4 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 1.14.5 Medical Equipment Assembly | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 3 years |
| | 1.14.6 Manufacture of optical instruments or photographic equipment or magnetic and optical media items | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 3 years |

| ተ.ቁ | የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የአሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|---|
| | **1.15 የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ** | | |
| | የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን ማምረት | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | **1.16 የማምረቻ/አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎችና ዕቃዎች ኢንዱስትሪ** | | |
| | 1.16.1 ለሁለገብ አገልግሎት ሥራ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ማምረት | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.16.2 ለልዩ አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎችን ማምረት | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | **1.17 የመጓጓዣ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች የትራንስፖርት መሣሪያዎችን ማምረት** | | |
| | 1.17.1 የሞተር ተሽከርካሪን(መኪና) ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.17.2 የመኪና አካላትን፣ተጎታችን እና/ወይም ከፊል ተጎታችን ወይም መለዋወጫዎችን እና ተጓዳኝ አካላትን ማምረት | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.17.3 በባቡር እና በትራም መንገድ የሚሄዱ ሎኮሞቲቮችን እንዲሁም ዘዋሪ እግር ያላቸውን ተሽከርካሪዎችን እና ጋሪዎችን ማምረት | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.17.4 የሞተር ብስክሌቶችን፣ ብስክሌቶችን እና ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎችን መፈብረክ | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.17.5 ጀልባዎችን መገንባት | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.18 የቤትና የቢሮ ዕቃዎች (ከሴራሚክ የሚሰሩትን ሳይጨምር) ማምረት | ለ 1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.19 የእደጥበብ፣ የገፀበረከት ዕቃዎች፣ አርቲፊሻል ጌጣጌጥ፣የሙዚቃ እና የስፖርት ዕቃዎችን ማምረት | ለ 1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 1.20 ከግብርና ጋር የተቀናጀ የማምረት ኢንዱስትሪ | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |

| Item No. | Investment Area | Addis Ababa and Oromia Special Zone surrounding Addis Ababa | Other Areas |
|---|---|---|---|
| | **1.15 Electrical Products Industry** | | |
| | Manufacturing of electrical products | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | **1.16 Production Machinery/ Service equipment and goods Industry** | | |
| | 1.16.1 Manufacture of general-purpose machinery | Exemption from Income Tax for 5 years | Exemption from Income Tax for 6 years |
| | 1.16.2 Manufacture of machineries used for different purposes | Exemption from Income Tax for 5 years | Exemption from Income Tax for 6 years |
| | **1.17 Manufacture of Transport vehicles and other transport equipment** | | |
| | 1.17.1 Manufacture of motor vehicles | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 1.17.2 Manufacture of vehicle components, trailers and/or semi-trailers or spare parts and accessories | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 3 years |
| | 1.17.3 Manufacture of railway or tram locomotives as well as trolley cars and wagons | Exemption from Income Tax for 5 years | Exemption from Income Tax for 6 years |
| | 1.17.4 Manufacture of motor bicycles, bicycles and three wheel vehicles | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 3 years |
| | 1.17.5 Building of boats | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 3 years |
| | 1.18 Manufacture of office and household furniture (excluding those made from ceramics) | Exemption from Income Tax for 1 year | Exemption from Income Tax for 2 years |
| | 1.19 Manufacture of arts and gift articles, artificial jewelry, musical and sports items | Exemption from Income Tax for 1 year | Exemption from Income Tax for 2 years |
| | 1.20 Integrated manufacturing industry with agriculture | Exemption from Income Tax for 4 years | Exemption from Income Tax for 5 years |

| ተ.ቁ | የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|---|
| | 1.21 የኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፓርክን ጨምሮ፣ ማልማት እና የማከራየት ሥራዎች | ለ 10 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 15 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 2 | **2. ግብርና** | | |
| | **2.1 የእርሻ ልማት** | | |
| | **2.1.1 የዓመታዊ ሰብሎች ልማት** | | |
| | 2.1.1.1 የብርዕና የአገዳ ሰብሎች ወይም የሸንኮራ ማልማት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| | 2.1.1.2 የቅባት እህሎች ማልማት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| | 2.1.1.3 የጥራጥሬ እህሎች ማልማት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ 3 ዓመት ግብር ነፃ መሆን |
| | 2.1.1.4 አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ እጽዋት እንዲሁም የተረጋገጠ ምርጥ ዘር ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| | 2.1.1.5 የጭረት ሰብሎችን ማምረት እና ማዘጋጀት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| | 2.1.1.6 የእንስሳት መኖ ማልማት፣ለመድኃኒትነት፣ ለሽቶ፣ ለቅመምነት እና ለመሳሰሉት የሚሆኑ ሰብሎችን ማልማት | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| | **2.1.2 የመካከለኛ ጊዜ ቋሚ ተክሎች ማልማት** | | |
| | 2.1.2.1 አበባ ማልማት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| | 2.1.2.2 በርበሬና ቅመማ-ቅመም ማልማት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| | **2.1.3 ቋሚ ተክሎች ልማት** | | |
| | 2.1.3.1 ቡና እና/ወይም ሻይ ቅጠል ማልማት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| | 2.1.3.2 የጎማ ዛፍ፣ ጀትሮፋ እና/ወይም ፓልም ልማት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ 6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| | **2.2 የእንስሳት ሀብት ልማት** | | |
| | 2.2.1 የቤት እንስሳት እና/ወይም የዱር እንስሳት እርባታ እና ተዋፅኦ ልማት(ማደለብን ሣይጨምር) | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |

| Item No. | Investment Area | Addis Ababa and Oromia Special Zone surrounding Addis Ababa | Other Areas |
|---|---|---|---|
| | 1.21 Development and rental of Industry Park including ICT Park | Exemption from Income Tax for 10 years | Exemption from Income Tax for 15 years |
| 2 | **2. Agriculture** | | |
| | **2.1 Agricultural development** | | |
| | **2.1.1 Annual crop production** | | |
| | 2.1.1.1 Growing of cereals, leguminous crops or sugarcane | No Income Tax Exemption | Exemption from Income Tax for 3 years |
| | 2.1.1.2 Growing of oil seeds | No Income Tax exemption | Exemption from Income Tax for 3 years |
| | 2.1.1.3 Growing of cereals | No Income Tax exemption | Exemption from Income Tax for 3 years |
| | 2.1.1.4 Growing vegetables, fruits, herbs as well as certified seeds | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 2.1.1.5 Growing and processing fiber crops | No Income Tax exemption | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 2.1.1.6 Growing animal feeds, medicinal crops, aromatic, spices and other crops for similar purposes | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 3 years |
| | **2.1.2 Growing of Medium-Term Crops** | | |
| | 2.1.2.1 Growing of flowers | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 2.1.2.2 Growing of pepper and spices | No Income Tax exemption | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | **2.1.3 Growing Permanent Crops** | | |
| | 2.1.3.1 Coffee and/or tea plantation | No Income Tax exemption | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 2.1.3.2 Rubber tree, Jatropha and/or palm | No Income Tax Exemption | Exemption from Income Tax for 6 years |
| | **2.2 Animal Production** | | |
| | 2.2.1 Farming domestic and/or wild animals and production of their outputs (excluding fattening) | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 4 years |

| ተ.ቁ | የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|---|
| | 2.2.2 የዶሮ እና/ወይም አዕዋፋት እርባታ እና ተዋፅኦ ልማት | ለ 1 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| | 2.2.3 ንብ ማነብ/ማር ማምረት | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| | 2.2.4 የሐር ትል ማልማት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| | 2.2.5 በሰው ሰራሽ ኩሬ የባህር እንስሳት/ዓሳ ማምረት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| | 2.3 የተጣመረ ግብርና /የእርሻና እንስሳት/ ልማት | ለ 3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| | 2.4 ደን ማልማት እና ተዛማጅ ሥራዎች | ለ 8 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን | ለ 9 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| 3 | **የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት መስኮች**<br>1. የሶፍትዌር ልማት<br>2. የዳታ ማዕከል እና ክላውድ አገልግሎት<br>3. ቢዝነስ አውትሶርሲንግ ፕሮሰስ<br>4. የስታርታፕ ልማት አገልግሎት<br>5. የምርምር፣ ፈጠራ እና የማበልጸግ ወይም የማልማት ሥራ | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ መሆን |
| | 6. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| | 7. በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አስቻይነት የሚከናወኑ ሌሎች አገልግሎቶች | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 4 | **የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት፣ ማስተላለፍና ማሰራጨት** | | |
| | 4.1 የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 4.2 የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፍ፣ ማከፋፈል | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

| Item No. | Investment Area | Addis Ababa and Oromia Special Zone surrounding Addis Ababa | Other Areas |
|---|---|---|---|
| | 2.2.2 Farming of chicken and/or birds and production of their outputs | Exemption from Income Tax for 1 year | Exemption from Income Tax for 2 years |
| | 2.2.3 Farming of bees/ producing honey | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 2.2.4 Production of silk | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 2.2.5 Fish farming in artificial ponds (aquaculture) | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 2.3 Mixed (crop and animal) farming | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 2.4 Forestry and related activities | Exemption from Income Tax for 8 years | Exemption from Income Tax for 9 years |
| 3 | **Information and Communication Technology Development**<br>1. Software development<br>2. Data center (bank) and cloud service<br>3. Business outsourcing process<br>4. Startup development Service<br>5. Research, innovation, enrichment and development works | Exemption from Income Tax for 4 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 6. Information technology service | No income tax exemption | No income tax exemption |
| | 7. Other services rendered using information technology as enabler | No income tax exemption | No income Tax exemption |
| 4 | **Electricity Generation, Transmission and Distribution** | | |
| | 4.1 Electricity generation | Exemption from Income Tax for 4 years | Exemption from Income Tax for 5 years |
| | 4.2 Electric power transmission and distribution | Exemption from Income Tax for 3 years | Exemption from Income Tax for 4 years |

| ተ.ቁ | የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|---|
| 5 | **ሆቴልና ቱሪዝም** | | |
| | 5.1 የኮከብ ደረጃ ያለው ሆቴል/ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ/፣ ሞቴል፣ሎጅ | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| | 5.2 የኮከብ ደረጃ ያለው ሬስቶራንት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| | 5.3 የአስጎብኚነት አገልግሎት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 6 | **የኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት** | | |
| | 6.1.1 ኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| | 6.1.2 የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| | 6.1.3 የማዕድን፣ የነዳጅ እና የጂኦተርማል ቁፋሮ | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 7 | **የትምህርት እና ስልጠና**<br>7.1 የሁለተኛ ደረጃና ከፍተኛ ትምህርት<br>7.2 የመዋዕለ ህፃናት፣ የአንደኛ ደረጃና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ<br>7.3 የቴክኒክና ሙያ ስልጠና (ስፖርትና ጨምሮ) አገልግሎት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 8 | **የጤና አገልግሎት**<br>8.1 ቴርሸሪ የልዩ ሆስፒታል አገልግሎት (ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን) | ለ 2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | 8.2 የሆስፒታል አገልግሎት<br>8.3 የምርመራ ማዕከል አገልግሎት<br>8.4 የክሊኒክ አገልግሎት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |

| Item No. | Investment Area | Addis Ababa and Oromia Special Zone surrounding Addis Ababa | Other Areas |
|---|---|---|---|
| 5 | **Hotel and Tourism** | | |
| | 5.1 Star-designated hotel (including resort hotel) motel, lodge | No Income Tax Exemption | No Income Tax Exemption |
| | 5.2 Star-designated restaurant | No Income Tax Exemption | No Income Tax Exemption |
| | 5.3 Tour Operation | No Income Tax Exemption | No Income Tax Exemption |
| 6 | **Construction Contracting** | | |
| | 6.1.1 Construction contracting | No Income Tax Exemption | No Income Tax Exemption |
| | 6.1.2 Water well drilling | No Income Tax Exemption | No Income Tax Exemption |
| | 6.1.3 Mineral, petroleum and geothermal exploration drilling | No Income Tax Exemption | No Income Tax Exemption |
| 7 | **Education and Training**<br>7.1 Secondary and higher education<br>7.2 Kindergarten, elementary and junior secondary school<br>7.3 Technical and vocational (including sports) training service | No Income Tax Exemption | No Income Tax Exemption |
| 8 | **Health Services**<br>8.1 Provision of tertiary specialized hospital service (to be determined by a Directive of the Ministry) | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 3 years |
| | 8.2 Provision of hospital service<br>8.3 Provision of diagnostic service<br>8.4 Provision of clinical service | No Income Tax Exemption | No Income Tax Exemption |

| ተ.ቁ | የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|---|
| 9 | **የአርኪቴክቸር እና የኢንጂነሪንግ ሥራዎች፣ የቴክኒክ ምርመራና ትንተና** | | |
| | 9.1 የአርኪቴክቸር እና የኢንጂነሪንግ ሥራዎች፡ እና ተዛማጅ የቴክኒክ ማማከር አገልግሎት<br>9.2 የቴክኒክ ምርመራ እና ትንተና<br>9.3 የጂኦፊዚክስ እና የላቦራቶሪ አገልግሎት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 10 | የሎጂስቲክስ አገልግሎት<br>10.1 የቀዝቃዛ መጋዘን አገልግሎት<br>10.2 የብትን ጭነት (ሳይሎ) መጋዘን አገልግሎት | ለሁለት አመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት | ለአራት አመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት |
| | 10.3 የደረቅ ወደብ አገልግሎት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለአምስት አመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት |
| 11 | **ተሽከርካሪን የማይጨምር የካፒታል ዕቃዎች ኪራይ** | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 12 | የገቢ ንግድ<br>ቡታ ጋዝ ወይም ቢትመን ማስመጣት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 13 | **የጅምላ ንግድ**<br>ነዳጅና የነዳጅ ምርቶችን ማቅረብ እና የራስን ምርት በጅምላ መሸጥ \ | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |

| Item No. | Investment Area | Addis Ababa and Oromia Special Zone surrounding Addis Ababa | Other Areas |
|---|---|---|---|
| 9 | **Architectural and Engineering Works, Technical Testing and Analysis** | | |
| | 9.1 Architectural and engineering works and related technical consultancy services<br>9.2 Technical survey and analysis<br>9.3 Geophysics and laboratory services | No Income Tax Exemption | No Income Tax Exemption |
| 10 | **Logistics Services** | | |
| | 10.1 Cooling Warehouse Services<br>10.2 Silos Warehouse Services | Exemption from Income Tax for 2 years | Exemption from Income Tax for 4 years |
| | 10.3 Dry Port Services | No Income Tax Exemption | Exemption from Income Tax for 5 years |
| 11 | **Capital Goods Leasing, excluding Leasing of Motor Vehicles** | No Income Tax Exemption | No Income Tax Exemption |
| 12 | **Import Trade**<br>Importation of LPG and bitumen | No Income Tax Exemption | No Income Tax Exemption |
| 13 | **Wholesale Trade**<br>Supply of petroleum and petroleum products as well as wholesale of own products | No Income Tax Exemption | No Income Tax Exemption |